የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ሚያዚያ 1 ቀን 2001 ዓ.ም

# በመፈንቅለ መንግሥት ሽፋን አፈናው ተጧጡፏል

የወያኔ አገዛዝ ፖለቲካ አሳፋሪና አረመኔ ከመሆን አልፎ አንዳንዴም በተራ ቧልትነት ሊፈረጅ መቻሉን ሰሞኑን 35 ሰዎች መፈንቅለ መንግስት ሊያደርጉ ሲያሴሩ ይዣለሁ በሚል ያስተጋባው ጩኸት ያጋልጠዋል:: በዚህ ክስ መሰረት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቃዋሚ ሀይሎችን በሽብርተኝነትፈርጆ ሊያሳጣና ሊያስጠላ ከመጣሩ ሌላ በሀገር ውስጥ ደግሞ ተቃዋሚዎችን በተለይም በራሱ ሠራዊት ውስጥ እየባሰ በመጣው ቀውስ የተነሳ ተፃራሪዬ ያላቸውን በማፈስና በማገት ላይ መሆኑተረጋግጧል:: ኢሕአፓ ይህን አፈና በጥብቅ ያወግዛል::

መፈንቅለ መንግስት ተብሎ የቀረበው ክስ በመሰረቱ አስቂኝ መሆኑ ከራሱ ዘገባ የሚታይ ነው:: በተወሰኑ ክላሽኖች÷ሽጉጦችና ቻይና ቦምቦች ብቻ ያውም ተያዙ የተባሉት ብዙዎቹ በአሁኑ ጊዜ በሠራዊቱ ቁልፍ ቦታን ባልያዙበት ሁኔታ መፈንቅል ይደረጋል ብሎ መገመት የሚቻል አይደለም:: ከዚህ ባሻገር ግን ድርጅቶች በህቡዕ መታገል የተገደዱት በራሱ በወያኔ ፀረ ዴሞክራሲነት የተነሳ አፈናው አስገድዷቸው መሆኑ የሚታወቅ ነው:: ድርጅቶች የሁለገብ ትግልን አማራጭ የግድ መከተል የመረጡትም በራሱ በወያኔ ፀረ ሰላምነትና ፀረ ዴሞክራሲነት መሆኑ ደግሞ ምስጢር አይደለም:: በሰላማዊ መንገድ ሊታገሉ የጣሩና በምርጫ ሳይቀር ሊወዳደሩ የሞከሩትም በ1997 ዓ.ም. በደረሰው ፍጅትና አፈና አማካኝነት የወያኔን አሉታዊ ምላሽ አግኝተዋል:: ለወያኔ አገዛዝ ተለጣፊ ሆነው ሊያገለግሉ የወሰኑ ካልሆነ በቀር ማንኛውም ሀቀኛ ሀገር ወዳድ ድርጅት የወያኔን አገዛዝ በሁለገብ ትግል ነቅንቆና አጥቅቶ መጣል እንዳለበት ግልፅ ነው:: ኢሕአፓ ይህን አቅዋሙን ግልፅ አድርጎ የወያኔን አገዛዝ በትግል ለመገርሰስ ሲደራጅና ሲያደራጅ መቆየቱም ምስጢር አይደለም:: በህቡዕ የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶችም ለወያኔ አገዛዝ ሰላዮችና ሰርጎ ገቦች ሰለባ እንዳይሆኑ ማሳሰቢያና ከተመክሮውም ያገኘውን ሁሉ ከማስተላለፍ ተቆጥቦ አያውቅም::

በኢትዮጵያ ዋናው ሽብርተኛ ኃይል የወያኔ አገዛዝ መሆኑ በመረጃ የተረጋገጠ ነው። ሕዝብና ድርጅቶች የሚወስዱት እርምጃ ካለም ፍትህዊና የመከላከል መሆኑ አያከራክርም። በወያኔ አገዛዝ የተወነጀለው ድርጅት ስለራሱ እንቅስቃሴ ምላሽ መስጠት የሚችል ሲሆን በዚህ ክስ ሽፋን የወያኔ አገዛዝ እያካሄደ ያለውን አፈናና እገታ ኢሕአፓ በጥብቅ ያወግዛል። የታሰሩትም ሁሉ እንዲፈቱ እየጠየቀ በተለይም በዝምድና መሰረት የተያዙት የ80 ዓመት አዛውንት በአስቸኳይ እንዲፈቱ ይላል። የወያኔ ቡድን ክስን ከአባት ወደ ልጅ ወይም ከልጅ ወደ አባት አሸጋግሮ መበቀል ልምዱ ነውና ይህንንም አጥብቆ ማውገዝ ያስፈልጋል። ከዚህ ባሻገር ግን ድርጅቶች የወያኔን አገዛዝ ለመጣል አሁንም በጥንቃቄና በምር ለሁለገቡ ትግል መዘጋጀትና በሙያተኛነትም መደራጀት እንዳለባቸው ኢሕአፓ ያምንበታል።

አፈናው ይቁም!
የታሰሩት ሁሉ ይፈቱ!
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com

Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France